# ከህዝብ ውክልናና ዕውቅና ውጪ የሚደረግ
# የድንበር ድርድር በህዝባችን ተቀባይነት አይኖረውም!

ግንቦት 10. 2000 ዓ.ም (May 18.2008)

ሀገራችን ኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት በውጪ ጠላቶች ዳር ድንበሯ ሊደፈር ቢሞከርም በጀግኖች ልጆቿ ቆራጥ ተጋድሎና መስዋዕትነት ለዘመናት ተከብሮ እንደቆየ በታሪክ የተዘገበ ሃቅ ነው::

ባለፉት አስራስባት ዓመታት የኢህአዲግ አምባገነናዊ መንግስት የአገሪቱን ሉአላዊነት የሕዝቧን ጥቅምና አንድነት የሚፃረሩ ውሎችንና ስምምነቶችን ሲያደርግ ይህ የመጀመሪያው አይደለም:: ሀገሪቱን ወደብ አልባ ያደረጋት ውልና ቁጥራቸው ከሰባ ሺህ በላይ ለሆኑ ኢትዮጵያውያን መቀጠፍ ምክንያት የሆነውን የባድመን ድል አሳልፎ የሰጠው ስምምነት ለናሙና የሚጠቀሱ ሲሆኑ በሱማሊያ በየቀኑ ያለምክንያት እየረገፈ ያለው የወጣት ኢትዮጵያውያን ህይወት ለገዢው ቡድን የስልጣን ዘመን ማራዘሚያና የግለሰቦች ጥቅም ማካበቻ ከመሆን ባሻገር ለኢትዮጵያዊነትና ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም የሚያስገኘው ምንም ፋይዳ የለም:: እንዲያውም በተቃራኒው አትዮጵያንና ኢትጵየዊነትን ለማጥፋት ቆርጦ የተነሳ ለመሆኑ ብቻ ነው ማረጋገጫ ሊሆን የሚችለው::

እንግዲህ ከዚህ ተሞክሮ በመነሳት የሰሞኑን የኢትዮ-ሱዳንን ድንበር ችግር ስንመለከት የኢህዲግ አምባገነን መንግስት ምንም ችግር እንደሌለ ሊያስተባብል ቢሯሯጥም በአካበቢው ነዋሪ በሆኑ ወገኖቻችን ላይ የሱዳን ጦር ያደረሰውን በደልና በዚሁ ወራሪ ኃይል ታፍነው መወሰዳቸውን ከተጠቂዎቹ አንደበትና አመኔታ ካላቸው ሚዲያዎች ለማረጋገጥ ችለናል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ከሱዳን ዲፕሎማቶችና ከዜና አውታሮችም ሂደቱ በግልጽ የተረጋገጠ ሆኖ ሳለ አንዳንድ አፍቃሪ ኢህአዲግ መድረኮችና ሚዲያዎች እንደተለመደው የክህደት ፕሮፓጋንዳቸውን ተያይዘውታል:: ከነዚህ ጭብጦች በመነሳት አሁንም የኢትዮጵያ ህዝብ ሳያውቀውና ሳይመክርበት የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅምና የድንበሯን አንድነት በጣም በሚጎዳ መልኩ አምባገነኑ የኢህአዲግ መንግስት ውል ሳይዋዋል እንዳልቀረ ለማመን ተገደናል::

ለወትሮው በሚረቡና በማይረቡ ጉዳዮች የሚነታረከው የወያኔ ፓርላማ የሀገርን ሉአላዊነት የሚያክል ታላቅ ጉዳይ ቢያንስ ለይስሙላ እንኳን ለውይይት አለማቅረቡና በዜና አውታሮችም እንዳይነገር መሻቱ በሀገራችን የሚኖሩት ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ስለሚመለከታቸው ስለሀገራቸውም ሆነ ስለአካባቢያቸው ወቅታዊ ሁኔታዎች እውቀትና ግንዛቤ እንዳይኖራቸው በመፈለግና ከህዝቡ በስተጀርባ በህቡዕ የሚሰሩት ደባዎች የሕዝብ ቅዋሜ እንዳይደርስባቸው ከማጤን የተነሳ መሆኑን ይጠቁማል::

በመጨረሻ እኛ ስማችን ከዚህ በታች የተዘረዘረው በጀርመን ሀገር የምንኖር የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች የአመራር ክፍል አባላት ዛሬ ሜይ 18 2008 ባደረግነው ስብሰባ በተለያዩ የሀገራችን ወቅታዊ ችግሮች ዙሪያ በስፋት ከተወያየን በኃላ የሚከተለውን የጋራ የአቋም መግለጫ አውጥተናል::

1. የኢትዮጵያ ህዝብ ከሁሉም የአጎራባች ሀገሮች ህዝብ ጋር በሰላምና በመከባበር መኖርን ይፈልጋል:: ስለሆነም ሰላምና ዲሞክራሲን አስፍኖ ከድህነትና ኋላቀርነት ለመውጣት በሚያደርገው ትግል ይህ እጅግ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ መሆኑን ጠንቅቆ ይረዳል:: በድንበሮች አከባቢ ችግሮች ሲፈጠሩ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ተጨባጭ የሆኑትን የታሪክ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን በማገናዘብና ዋና ባለጉዳይ ከሆነው ህዝባችን ጋር በመመካከር የሀገራችንን ጥቅም በማይጎዳ መልኩ በሰላም፤ በድርድርና በዲፕሎማሲ የሁለቱንም ሀገሮች መልካም ጉርብትና ባገናዘበ መልኩና ግልጽነት በተሞላባቸው ስምምነቶች እልባት ማግኘት እንዳለባቸው በጽኑ እናምናለን::

   ከዚህ ውጪ ያለህዝብ ውክልና፤ ከህዝባችን ጀርባ በማን አለብኝነትና ከድንበር ጉዳይ ጋር ባልተያያዘ ሌላ የፖለቲከ ጥቅም ስሌት የሚደረጉ የእከክልኝ ልከክህ ስምምነቶች ግን በሁለት ወንድማማች ህዝቦች መካከል አላስፈላጊ የሆኑ ግጭቶችን እንደሚቀሰቅሱና ይህም በታሪክና በህዝብ ፊት ተጠያቂነትን እንደሚያስከትል በስልጣን ላይ ላለው የኢህአዲግ አምባገነናዊ መንግስት ለማስገንዘብ እንወዳለን::

2. በሀገራችን ነፃነትን፤ ፍትህን፤ ሰላምንና እኩልነትን ለማስፈን በሚደረገው ትግል ዙሪያ ከተሰለፋችሁት የዲሞክራሲ ኃይሎችና ከኢትዮጲያ ህዝብ ጋር እንደተሰለፍን ሁሉ ሉዓላዊነታችንንም ለማስከበር በሚደረጉት እንቅስቃሴዎች ሁሉ በጋራ እንደምንቆም ለማረጋገጥ እንወዳለን::

የሀገራችንን ዳር ድንበር ለማስከበር የአባቶቻችን አደራ አለብን!

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

---

በኑርንበርግና አካባቢው የቅንጅት ድጋፍ ማህበር

የቅንጅት ድጋፍ ድርጅት በኖርድራይን ቬስትፋለን ጀርመን

በሙኒክና አካባቢዉ የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ደጋፊ ግብረኃይል

---